# በስቶክሆልም የኢትዮጵያ ኤምባሲ የመንግሥት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ

በአገራችን የመንግሥት ሠራተኛውንና ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የከተማ ነዋሪ የቤት ባለቤት ለማድረግ መንግሥት በክልሎች እና በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በ20/80 ኮንዶሚኒየም ቤቶች ኘሮግራም የመኖሪያ ቤቶች ገንብቶ ለነዋሪዎች ሲያስረክብ ቆይቷል፡፡

የከተሞች የመኖሪያ ቤት ፍላጐት በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ፕሮግራሙን በማስፋት በ10/90፣ በ20/80 እና 40/60 ኘሮጀክቶች እንዲሁም በማህበራት ተደራጅተው ለሚቀርቡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ገንብቶ ለማቅረብ ምዝገባ ተካሂዶ በአሁኑ ጊዜ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የመኖሪያ ቤቶች ለነዋሪዎች ማስረከብ የተቻለ ሲሆን ቀሪውን የመኖሪያ ቤት ግንባታ በማጠናቀቅ ለማስረከብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ የዚህ ኘሮግራም አካል እንዲሆን ለማድረግ መንግሥት የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቶ በአሁኑ ወቅት የጋራ መኖሪያ ቤት ኘሮግራም ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በኩል ምዝገባ እንዲከናወን መመሪያ ተላልፏል፡፡

በዚሁ መሠረት ኤምባሲያችን በጋራ የመኖሪያ ቤት ኘሮግራሙ በግልም ይሁን በማህበር ተደራጅተው የቤት ባለቤት መሆን ለሚፈልጉ በስዊድን፣ በኖርዌይ፣ በዴንማርክ፣ በፊንላንድና አይስላንድ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ምዝገባ ለማካሄድ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን ከምዝገባው በፊት በምዝገባ ሂደቱ ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲፈጠር የኤምባሲውን ድረ ገጽና ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ዝርዝርና ግልጽ የሆነ መረጃ (የምዝገባ መስፈርቶች፣ የቤቶች አይነትና ስፋት፣ የግንባታ ዋጋ ግምት፣ የባንክ አካውንት አከፋፈት፣ የክልሎች ሞዴል የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ፣ ዝቅተኛው የአንድ ማህበር አባላት ብዛት፣ የዲዛይንና ግንባታ ሁኔታን) ከዚህ እንደሚከተለው እያቀረብን፣ ከዚህ በተጨማሪ ምዝገባውን ከመጀመራችን በፊት ትክክለኛና የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖር በስቶክሆልም፣ ኦስሎ፣ ኮፐንሃገንና ሄልሲንኪ ከተሞች በመኖሪያ ቤት ኘሮግራምና የምዝገባ ሂደት ላይ በቅርቡ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በየከተማው ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጋር ውይይት በማካሄድ በአጠቃላይ ፕሮግራሙ ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ምዝገባ እንደምንገባ ከወዲሁ እናሳውቃለን፡፡

for more information pls. follow the following link

http://ethemb.se/diaspora/opportunities-for-diaspora/housing-programs/